# ቨርጂኒያ የሚገኘው የሐመረ ኖህ ኪዳነ ምሕረት ቤተክርስቲያን ሰበካ ጉባኤ አመራር ‘ከረስሊንግ’ ባሻገር ህልውናውን አስከበረ

“ለሁሉም ጊዜ አለው” አባቶቻችንም መሰንበት ደጉ ሰው ከቆየ ብዙ ያያል ይላሉ። እኛም እግዚአብሔር እንደፈቀደ በጊዜው እያየን ነው። ነፍሱን ይማርና ታላቁ ኢትዮጵያዊ የኪነጥበብ ፈርጥ (ጋሼ) ሎሬት ፀጋየ ገብረመድሕን ስለዛች ስለሚወዳት አገሩ ቤተክርስቲያኑና ሕዝቡ የደረሰባቸውን በደል አንባውን እያፈሰሰ “ሁሉም ዝም” ስንፈርስ ዝምታ እስከመቼ ብሎ ነበር። አፈር ይቅለልህ። አንተ የጥበብ ሰው ድምፅህ ከመቃብር በላይ ሰሚ አግኝቶ ዝምታው ተንዱል።የፈጀውን ጊዜና የበላውን ሰው በልቶ።

አፈር መስኮት የለው ኖረህ ብታይልን ምንኛ ደስ ባለን። ይኸው ያንተው ጥሪ ቆየና አድሮ ውሎ መሠረቱን ጥሎ የቨንጂኒያ ሐመረ ኖህ ኪዳነ ምሕረት ቤተክርስቲያን ምዕመናና ሰበካ ጉባኤ አመራር ስለቤተክርስቲያናችን አንድነት እውነቱን እንዳይናገሩ ከተሸበቡበት ይሉኝታና፣ መሰሪ ቤተክርስቲያኗን በተዋህዶ ስም፣ በወንጌል ስም ለምድ ከለበሱ ተኩላዎች፣ በዓለም ቅጠል ከተሸፈኑ አንዳንድ ሆድ አደር ሰባኪያን ተረት ተረት የሰበካ ፈሊጥ ወጥተው፤ አምላካችን እግዚአብሔር በፈቃዱ ለህሕይወታቸው ኀይልን ሰጥቷቸው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን ከደረሰባት የመከፋፈልና የመለያየት አደጋ ለመታደግ ከፀፀት ባሻገር ጥረታቸውን ቀጥለው የኪዳነ ምሕረት ሰበካ ጉባዔ አመራር በቤተክርስቲያኗ አመራር ቄስ አማካይነት የቀረበላቸው ‘ፕሮፖዛል’ ረቂቅ ሀሳብ ቤተክርሲቲያኗን በግለሰቡ ስር እንደፈለጉ የሚያደርግና ከዚህ ቀደም ልክ በደብረ ምሕረት ቅዱስ ሚካኤል በተክርስቲያን በአባ መላኩ “መዋቅረ ዘህውከት” እንደታየው አይነት መዕመናኑንና ቤተከስቲያኑን የሚለይ የሁከት መዋቅር ስልት አዘጋጅተው በመቅረባቸው፣ የሰበካ ጉባኤው አመራርም “እግዚአብሔርስ የሰላም አምላክ እንጅ የሁከት አምላክ አይደለምና” 1ኛ ቆሮ 14፡33 በማለት ይህ አዋኪና መሰሪ ተግባር ቤተክርስቲያናችንን ለሌላ ከፋፋዮች አሳልፎ ለመስጠት የተቀነባበረና የተውጠነጠነ፣ የግለሰብ ንብረት የሚያደርጋት “ፕሮፖዛለ ህውከት” ነው በማለት ውድቅ አድርጎ ህልውናውን አስከብሯል።

የቤተክርስቲያኗ አስተዳዳሪ ከሆኑት ቄስ ጋ አብረው ረቂቀ ሃሳቡን በማቀነባበርና ተለጣፊ ቡድን ለማቋቋም እራሳቸውንም በውስጡ በማካተት በ”ጄኔራል” ስም የሚጠሩት ግለሰብ በሰበካ ጉባኤው አመረር ጠንካራ ተቃውሞና ትችት እንዲሁም እዚህ ላይ ልንጠቅሳቸው የማንፈቅዳቸው የቃላት መወራወርና በተለይም ረቂቅ ሐሳቡን ያቀረቡት “በሉት” የተባሉትን ገንዘብ እንዲመልሱ ነገሩ ከሮ የከፋ ደረጃ ደርሶ ነበርና፣ አባቶቻችን ሽማግሌ አታሳጣን እንዲሉ በስብሰባው ከነበሩት ነገር ግን በረቂቀ ሃሳቡም ይሁን እስከአሁ ድረስ የራሳቸውን ለፍተው ከመለገስ በቀር በሌሎች ጥቅማጥቅሞች እራሳቸውን ካልጨመሩት በደሳሳ ጎጆ ከሚገኙት የ84 ዓመቱ አዛውንት ካህን የሃዲስና የብሉይ፣ የቅኔያት ሊቅና መምህር የሆኑት በዚህ የከረረ ሪስሊንግ ቀረሽ ውዝግብ በሽምግልና ክፉውን ነገር በማብረድ፣ እውነት መስመር

እንዲይዝ በማድረጋቸው እሰየው አሁንም እንዳባቶቻችን የእውነት የሃገር ሽማግሌ አታሳጣን እያልን ለሽማግሌው ካህን አባታችን እረጅም እድሜና ጤና እየተመኘን ምስጋናችንን እያቀረብን ሽምግልናውን "ችሎት ዘማንዴላ ወመጋቢ አእላፍ መክብብ አጥናው" ብለነዋል።

የቨርጂኒያ ሐመረ ኖህ ኪዳነ ምሕረት ሰበካ ጉባኤ አመራር ያሉብትንና የደረሰበትን ጫናዎች በእውነት ጭብጥነት በጣጥሶ በመውጣት ለአራት ወራት አዲስ አባባ በመሄድ ከቆዩ በኋላ የአራት ወር ደመወዝ እንዲከፈላቸው የቤተክርስቲያኑ አስተዳዳሪ ቄስ በመጠየቃቸው የሰበካ ጉባዔው አመራር ቄሱ ላልሰሩበት ደመወዝ አንከፍልም መፅሃፉም "ያልሰራ አይብላ ነው" የሚለው በማለት ክፍያውን አግዱል። ይህ እርምጃ ለሌሎች ቤተክርስቲያናትም ምሳሌ የሚሆን ነው። እዚህና እዛ እየዘለሉ እየመጡ አላግባብ ክፍያ ለሚደረግላቸው አስደንጋጭ መርዶ መሆኑን አስተውለናልና ገንዘቡን እኛ ምዕመናን ከስራ ስራ ተሯሩጠን የምንከፍላቸው መሆኑን አበክረው ሊገነዘቡትና ልብ ሊሉት ይገባል።የሐመረ ኖህ ኪዳነ ምሕረት ሰበካ ጉባኤ እርቅን የማይፈልጉትን ማንም ይሁን ማ የቤተክርስቲያኗን እርቅ ካልፈለገ በአባትነት ስም እንደማያስተናግዱ የፀና አቋም ይዘዋል።

በተለይም አባ ቀውስጦስ እርቅን ከማይሻው ያልሰከነና የአንድነት በሽተኛ ከሆነውና ቤተክርስቲያኗን ለመበታንን በመከፋፈል የቆመውና ከዚህ ቀደም የደብረ ገነት መድኃኔ ዓለም ቤተክርስቲያን ከላይ እስከ ታች "መናፍቃን ናቸው" በሚል መሰሪ የመበታተን ልክፍት ተልዕኮውን የጀመረው እራሱን "ብፁዕ" ብሎ በሚጠራው አባ አብርሃም ተብየው፣ "እፉኝት" ጋር የኪዳነ ምህረት ቤተክርስቲያንን ለማግባባትና አሳልፎ ለማሰጠት ግለሰቡን በአባትነት ብትቀበሉት በሚል ማደናገሪያ ፈሊጥ የተሞከረውን ሴራ በማክሸፍ ሰበካ ጉባኤው መሰሪዎች ያስቀመጡበትን እንቅፋት በአንድነት በመቆም እየገፈተረ በሰው ሳይመካ "የሚመካ በእግዚአሔር ይመካ" በማለት በፅናት ህልውናውን በማስከበር ለቤተክርስቲያን አንድነት የወሰደውን ቁርጠኛ እርምጃና የሃቅ መንገድ በማጠንከር የሰበካ ጉባዔ አመራር አባላት በሕብረት ተያይዘውተዋልና እኛም በርቱ "ወደኔ ጩኽ እኔም እመልስልሃለሁ" ኤር 33፡3 ይላልና፣ ወደ አምላካችን እግዚአብሔር ከመጮህና በፀሎት፣ በጾም ከመትጋት፣ ስለ እውነት ከመሟገት ጋር ትሩፋታችሁን ቀጥሉ።

ማጠቃለያ፤ ከፋፋይ ውግዘትን በመፀየፍ ለቤተክርስቲያናችን ለዕርቅና ሰላም ለፍቅር የምታደርጉትን እርምጃ ከማፈጠን ጥረታችሁ ጋር፣ የቤተክርስቲያንን አንድነት የማይሹ፣ ለመለያየቷ የቆሙ፣ ሆድ አደሮች፤ በወቅታዊ ስልታቸው እራሳቸው የአንድነት፣ የሕብረትና የፍቅር ጠላት አዋኪያን መናፍቅ ሆነው፤ ቃለ እግዚአብሔርን መናፍቅ የሚሉ፣ ሕገ እግዚአብሔር የጠበቀውን መንፈሳዊ የእግዚአብሔር ሰው "መናፍቅ" የሚሉትን ከአዲስ የቤተክርስቲያን የጥፋት ዕቅዳቸው ጋር አሳፍሯልና በአለም ዙሪያ የምንገኝ የተዋህዶ ወታደሮች በርቱ እንላለን።
ስለሁሉም ነገር እግዚአብሔር ይመስገን !

ከፍኖተ ጽድቅ ዘበኢትዮጵያ
ሰሜን አሜሪካ
ሰኔ 27 ቀን 2000 ዓ.ም.